viva
together for children




# እግዚአብሔር የሰራት ምድር: የኛ መኖሪያ

**ዓለም አቀፍ የቅዳሜና እሁድ የፀሎት ቀን ግንቦት 27-28**

**በአብዛኞቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ውስጥ የመጀመሪያው ዓረፍተ ነገር የሚጀምረው "በመጀመሪያ እግዚአብሔር..." በሚል ቃል ነው።**

ሥርዓትን አበጅቶ  ዓለምን የፈጠረው እግዚአብሔር ነው። አዳምን በምድር ላይ ያሉትን ፍጥረታት  እንዲንከባከብ ሄዋን ደግሞ የሱ ረዳት እንድትሆን በትዳር አጣመራቸው።

የዘንድሮው ዓለም አቀፍ የቅዳሜና እሁድ የፀሎት ቀን **ጭብጥ እግዚአብሄር በፈጠራት ዓለም ላይ እንደምንኖር  እርሱ የሰጠንን ይህችን አስደናቂ መኖሪያችንን መንከባከብ እንዳለብን ከግንዛቤ ያስገባ ነው።**
ይህችን ውብ መኖሪያችንን በዚህ ዘመን ላሉ ልጆች እንዲሁም ለሚመጣው ትውልድ ምቾት ደህንነት እና ፍቅር የተሞላባት እንድትሆን በጋራ የመስራት ግዴታ አለብን።

በዘንድሮው ዝግጅት ላይ ጸሎታችን የሚያተኩረው ለእግዚአብሔር ፍጥረታት አድናቆት መስጠትን፤ ፍጥረታትን ለመንከባከብ የሚረዱ ስራዎች እንዲሁም በተፈጥሮ ላይ    በደረሰ ጉዳት ሳቢያ ጉዳት የደረሰባቸው ልጆችን ለመደገፍ የሚያስችሉ በጋራ የሚሰሩ የመፍትሄ ስራዎች ላይ ይሆናል።

*ፍጥረት ሁሉ የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ በናፍቆት ይጠባበቃል። (ሮሜ 8፡19)*

---

## ከቪቫ ዋና ስራ አስፈፃሚ ከአቶ ፊል ግሪን የተላለፍ መልዕክት



**በታህሳስ 2022 ቪቫን በዋና ስራ አስፈፃሚነት ከተቀላቀልኩ ወዲህ የዚህን ዓመት ዝግጅት መልዕክት ለማስተላለፍ በመቻሌ በጣም ደስተኛ ነኝ። ይህ መልዕክት ልጆችን በማበረታታት በፀሎትና በምስጋና ቀዳሚ ሆነው እንዲመሩን ያለኝን ፅኑ ፍላጎት ያሳያል።**
*አምላኬ እግዚአብሔር ሆይ፤ ይህም ሆኖ የባሪያህን ጸሎትና ልመና ስማ፤ በዛሬው ዕለት ባሪያህ በፊትህ የሚያቀርበውን ጩኸትና ልመና አድምጥ። 1ነገ 8፤28*

**ባለፈው ዓመት በሃያ አምስት አገራት የሚገኙ ከ800,000 በላይ ልጆችና አዋቂዎች በዓለም ዓቀፉ የቅዳሜና እሁድ የፀሎት ዝግጅት ላይ ተሳትፈዋል።**
በዘንድሮውም ዝግጅት ላይ ካለፈው ዓመት የበለጠ ቁጥር ያላቸው ልጆች እግዚአብሄርን ስለ ፍጥረት በማመስገንና በተፍጥሮ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለማስቀረት በትብብር እንድንሰራ ሲፀልዩ ለማየት በጉጉት እየጠበኩ ነው።

## ብርሃን ከጨለማ ተለየ

**የመጀመሪያ ቀን**

**የንባብ ክፍል፤** ዘፍጥረት 1፤1_5

**ምስጋና፤** እግዚአብሄር በምድር ስርዓትን አደረገ።

በምሽት ጨለማ ላይ ስለሚበራው ብርሃን።

**ለተፈጥሮ እንክብካቤ፤** ከታዳሽ ኃይል የሚመነጭ የኤሌክትሪክ ኃይል

**የጋራ እንክብካቤ ለልጆች፤** ስጋት በሆነው የመጥፎ ባህሪ ጨለማ ላይ ክርስቶስ ኢየሱስ ብርሃን እንዲያበራ

*አምላኬና ንጉሤ ሆይ፤ ከፍ ከፍ አደርግሃለሁ፤ ስምህን ከዘላለም እስከ ዘላለም እባርካለሁ።*
*በየቀኑ እባርክሃለሁ፤ ስምህንም ከዘላለም እስከ ዘላለም አመሰግናለሁ። መዝ 145፤1_2*

**ተግባራት፤** ይሄን ሊንክ በመጫን https://youtu.be/EegzzyLlnZQ

በወ/ሮ ሙካያላ ሞይለር ዕገዛ የምድርን ሞዴል በመስራት ተለማመዱ።



## የውሃና ሰማይ መለያየት

**ሁለተኛ ቀን**

**የንባብ ክፍል፤** ዘፍ 1፤6_8

**ምስጋና፤** ዝናብን ስለሚያስገኙልን ደመናት እናመስግን

**ለተፈጥሮ የሚደረግ እንክብካቤ፤** ተገቢ የሆነ የውሃ አጠቃቀም ፤ ግድቦች፣መስኖ፣ የውሃ መሳቢያ ሞተር እና የውሃ ቧንቧዎች

**የጋራ እንክብካቤ ለልጆች፤** ለሁሉም ልጆች ንፁህና ያልተበከለ ውሃ

እግዚአብሔር ታላቅ ነው፤ እጅግ ሊመሰገንም ይገባዋል፤ታላቅነቱም አይመረመርም።
ሥራህን አንዱ ትውልድ ለሌላው ትውልድ ያስተጋባል፤ብርቱ ሥራህን ያውጃል።
ስለ ግርማህ ውበትና ክብር ይናገራሉ፤ መዝ 145፤3_5

**ተግባራት፤** የእግዚአብሄርን አስደናቂ ፍጥረታትን የሚገልፁ ስሞችን ዘርዝሩ

የዝናብ ውሃ ቀድታሁ መጠኑን ለኩ



## በዛፎች፣ አትክልትና ፍራፍሬ የተሞላች ምድር

**ሶስተኛ ቀን**



**የንባብ ክፍል፤** ዘፍ1፤9_13

**ምስጋና፤** መኖሪያ ስለሆኑልን ተራሮች እና ሸለቆዎች ምግብ ስለሆኑልን አትክልት እና ፍራፍሬዎች

**ለተፈጥሮ የሚደረግ እንክብካቤ፤** አፈሩን በማይጎዳ መልኩ እህል ማምረት የደን ጭፍጨፋን መከላከል።

**የጋራ እንክብካቤ ለልጆች፤** በቂ የአትክልትና ፍራፍሬ ምግቦች ለልጆች

ስለ ድንቅ ሥራህ ብርታት ይነጋገራሉ፤እኔም ስለ ታላቅነትህ ዓውጃለሁ።
የበጎነትህን ብዛት በደስታ ያወሳሉ፤ስለ ጽድቅህም በእልልታ ይዘምራሉ።
እግዚአብሔር ቸር ነው፤ ርኅሩኅም ነው፤ለቍጣ የዘገየ፣ ምሕረቱ የበዛ። መዝ 145፡6-8

**ተግባራት፤** ዛፎችን ትከሉ፣ የምግብ ዛፎችንም ትከሉ። ዛፎች በሚበዙበት ቦታ የእግር ጉዞ አድርጉ

## ቀን, ለሊት. ፀሐይ፣ ጨረቃ እና ኮከቦች

**አራተኛ ቀን**

**የንባብ ክፍል፤** ዘፍ 1:14-19

**ምስጋና፤** ስለፀሃይ ብርሃንና የተለያዩ ወቅቶች እንዲሁም ዓለማትን በቦታቸው ስለሚያስጠብቀው የመሬት ስበት ኃይል።

**ለተፈጥሮ የሚደረግ እንክብካቤ፤** ሰዎች በአየር ሁኔታ ላይ ያላቸውን ተፅዕኖ መቀነስ። አደገኛ የአየር ሁኔታ መከሰትን መቀነስ።



**የጋራ እንክብካቤ ለልጆች፤** እሳት፣ ድርቅና ጎርፍ በመሳሰሉ የተፈጥሮ አደጋ ጉዳት የደረሰባቸውን ልጆችና ቤተሰቦች መርዳት።

እግዚአብሔር ለሁሉ ቸር ነው፤ምሕረቱም በፍጥረቱ ሁሉ ላይ ነው።
እግዚአብሔር ሆይ፣ ፍጥረትህ ሁሉ ያመሰግንሃል፤ቅዱሳንህም ይባርኩሃል።ስለ መንግሥትህ ክብር ይናገራሉ፤
ስለ ኃይልህም ይነጋገራሉ፤በዚህም ብርቱ ሥራህን፣የመንግሥትህንም ግርማ ክብር ያስታውቃሉ።
መዝ 145፤9_12

**ተግባራት፤** ጨረቃና ከዋክብትን የመሳሰሉ የተፈጥሮ ፀጋዎችን ለመቃኘት የእግር ጉዞ አድርጉ።
በአነስተኛ ቡድን ሆናችሁ የጎርፍ አደጋን ለመቀነስ የሚያስችል ስራ መስራት።

## አሳና ወፎች _ ፍሬያማ ሁኑ

**አምስተኛ ቀን**

**የንባብ ክፍል፤** ዘፍ 1፤20_23



**ምስጋና፤** ስለ አሳዎችና ወፎች ውበት በሁሉ ነገር ተመጣጥኖ ስለተሰጣቸው መኖሪያ ለምግብነት መልካም ስጦታ ሆኖ ለእኛ ስለተሰጠን።

**ለተፈጥሮ የሚደረግ እንክብካቤ፤** ከመጠን ያለፈ የአሳ ማጥመድን የሚያስቀር አስተዳደር። ዘላቂ የሆኑ የግብርና አሰራሮች ጥቅም ላይ ማዋል።

**የጋራ እንክብካቤ ለልጆች፤** ሁሉም ቤተሰቦች በቂ የፕሮቲን ምግቦች ማግኘት እንዲችሉ። ልጆች ከምግብ አመራረት ጋር በተያያዙ በሽታዎች ከመያዝ እንዲጠበቁ።

መንግሥትህ የዘላለም መንግሥት ናት፤ግዛትህም ለትውልድ ሁሉ ጸንቶ ይኖራል።
እግዚአብሔር ቃሉን ሁሉ ይጠብቃል፤እግዚአብሔር የሚንገዳገዱትን ሁሉ ይደግፋል፤
የወደቁትንም ሁሉ ያነሣል።የሁሉ ዓይን አንተን በተስፋ ይጠብቃል፤አንተም ምግባቸውን በወቅቱ ትሰጣቸዋለህ። መዝ 145፤13-15

**ተግባራት፤** ወፎችን ለመቃኘት የእግር ጉዞ አድርጉ። የፕላስቲክ የተበከሉ አካባቢዎችን አፅዱ።
የተመጣጠነ ጤናማ ምግብ በጋራ አዘጋጁ።

## ሁሉም በመሬት ላይ የሚኖሩ ፍጥረታት፣ የቤት እንስሣት፣ የሰው ልጅ

**ስድስተኛ ቀን**

**የንባብ ክፍል፤** ዘፍ 1፤24_31

**ምስጋና፤** በመሬት ላይ ስለሚኖሩ ፍጥረታት እና የእርስ በርስ ግኑኝነታቸው። ስለ ሴትና ወንድ እንዲሁም ስለ ትዳርና በቤተሰብ ውስጥ ስለሚገኙ ልጆች

**ለተፈጥሮ የሚደረግ እንክብካቤ፤** ቁጥሩ እየጨመረ በመጣው የሰው ልጅ እና በእንስሣት መካከል ያለውን ፍላጎት ማመጣጠን የሚያስችል ጥበብ



**የጋራ እንክብካቤ ለልጆች፤** ትዳሮች በፍቅር፣ በመተሳሰብና በህብር የተጠበቁ እንዲሆኑ።
በትዳር ውስጥ የተወለዱ ልጆች እንክበካቤ ማግኘት እንዲችሉ።

አንተ እጅህን ትዘረጋለህ፤የሕያዋን ፍጥረታትንም ሁሉ ፍላጎት ታረካለህ። እግዚአብሔር በመንገዱ ሁሉ ጻድቅ፣
በሥራውም ሁሉ ቸር ነው። እግዚአብሔር ለሚጠሩት ሁሉ፤በእውነት ለሚጠሩት ሁሉ ቅርብ ነው።
ለሚፈሩት ፍላጎታቸውን ይፈጽማል፤ ጩኸታቸውን ይሰማል፤ ያድናቸዋልም። መዝ 145፤16-19

**ተግባራት፤** በሁሉም ፊደላት ያሉ የእንስሣት ስሞችን ተራ በተራ የመጥራት ጨዋታ ተጫወቱ።
የእጅ አሻራ በወረቀት ላይ በመቅረፅ ሁሉም የተለያየ መሆኑን አስተውሉ።

ሰባተኛ ቀን

## የእረፍት ቀን

**የንባብ ክፍል፤** ዘፍ፤2፤1_3

**ምስጋና፤** በሳምንት አንድ ቀን ለእረፍትና አምልኮ ላይ ለማተኮር እንዲውል ስላደረገው የእግዚአብሄር ዕቅድ

**ለተፈጥሮ የሚደረግ እንክብካቤ፤** እራሳችንን መንከባከብ፤ የሰው ልጆችን በሙሉ።

መልካም ልምዶችን ማዳበር ስራና እረፍትን ማመጣጠን እንዲሁም መዝናናት



**የጋራ እንክብካቤ ለልጆች፤** ልጆች ከቤተሰቦቻቸው ጋር መልካም ጊዜን በአረንጓዴ ስፍራዎች እንዲያሳልፉ

እግዚአብሔር የሚወድዱትን ሁሉ ይጠብቃል፤ክፉዎችን ሁሉ ግን ያጠፋል።
አፌ የእግዚአብሔርን ምስጋና ይናገራል፤ፍጡር ሁሉ ከዘላለም እስከ ዘላለም፤
ቅዱስ ስሙን ይባርክ። መዝ 145፤20_21

## እባካችሁ አብረን እንፀልይ

### 1. እግዚአብሄር ዓለምን ፈጥሯል



እግዚአብሄር ሆይ በቀን እና በምሽት ስላደረክልን ብርሀን እናመሰግንሀለን።

በቤቴ ስላለው ብርሃን አመሰግንሀለው። ምድርን ስለሚያረሰርሰው ዝናብ አመሰግንሀለው።

አቤቱ ታላቁ አምላካችን ሆይ ዝናብን ለሚያስፈልጋቸው ሁሉ እንድትሰጥ እለምንሀለው ፤

አንተ ሁሉን ቻይ ነህ። ምድርን ስለፈጠርካት እኔንም ስለፈጠርከኝ አመሰግንሀለው።

### 2. መኖሪያችን ምድር ተበክላለች



መልካም እና ፍፁም አድርገህ ምድርን ሰራሀት እኛ ግን በግድ የለሽነትና
በስግብግብነት ምድርን በከልናት ጌታ ሆይ ይቅር በለን!
ፈጣሪያችን እግዚአብሄር ሆይ ባህርን እንድንከባከብ አዘዝከን
እኛ ግን አቆሸሽነው ስለቸልተኝነታችን ምህረት አድርግልን።

### 3. ኢየሱስ መልሶ ይገነባል



ጌታ እግዚአብሄር ሆይ ችግሮችን የሚፈታና አስደናቂ ነገሮችን መፍጠር የሚችል
አዕምሮ ሰተህናል። ውብ አረንጓዴ ስፍራን እንዳዘጋጅ እርዳኝ አምላኬ እንዳንተ
መልካም ነገር መስራት እንድችል እርዳኝ። ለጠቃሚ ነገሮች መኖሪያ ስፍራ
እንዳዘጋጅ እና የማያስፈልጉ ነገሮችን በአግባቡ እንዳስወግድ እርዳኝ።

### 4. የእግዚአብሄር ዓለም የኛ መኖሪያ ወደ ነበረበት ተመልሷል



የአለም ፈጣሪ ሆይ ከአንተና ከህግህ ሸሽቼ ሳለሁ እኔን ለማግኘት ወደ ምድር
በድጋሚ ስለመጣህ አመሰግንሀለው። ኢየሱስ ሆይ በፍጥረታት ሁሉ ላይ
ኃይል ስላለህ አመሰግንሀለው። በዚህ ሁሉ ደግሞ በፍጥረታት ላይ ጠባቂ
አድርገህ ሾምከኝ እባክህ መልካም ጠባቂ እንድሆን እርዳኝ።